# ቀስተ ደመና

የሰላምና የወድማማችነት ድምፅ ሬድዮ ጋዜጣ

ቁጥር 4- 6 ታህሣሥ / የካቲት 1990

## ከአዘጋጅ ብዕር

የቀስተ ደመና ሬዲዮ፣ የሰላምና የወንድማማችነት ድምፅ ሥርጭቱን የጀመረው መስከረም 1 ቀን 1990 ዓ ም ነው።

ይህ ሁለተኛ መጽሄት የሚቀርበው ሬዲዮው ከጀመረ ከስድስተኛው ወር በኋላ ስለሆነ በቅርቡ ከተላለፉትና ባጭሩ ከቀረቡት የተወሰኑ ዜናዎች ሌላ፣ የመጽሄቱ ዋና ይዘት ለሃገራችን ወቅታዊ ጉዳዮችና ጥያቄዎች ቅድሚያ ትኩረት ለሰጡ ትችቶች፣ ትንተናዎች ወዘተ ነው።

መልካም ንባብ !

* ከሊንተን አፍሪካ........................1
* የፖለቲካ አጥቂነት....................2
* በአንድ ራስ አንድ ምላስ.........3
* ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ኬንያ.......5
* የእብዶች ሎጂክ ........................6
* በ 1992ቱ ምርጫ ላይ የተጠነሰሰው ሤራ....................7
* ህወሀት ለምርጫ ይዘጋጃል፤ ተቃዋሚዎችስ?.......................8
* የወያኔ መሰንበቻ ስልት..........10
* ከጋዜጦች አምድ.................... 11
* ዘመናዊ ባርነት...................... 15
* የወያኔን ኢትዮጵያ ሾላ በድፍን.......................17

ቀስተ ደመና (Radio Rainbow) የሰላምና የውንድማማችነት ድምፅ ሬዲዮ
በአጭር ሞገድ(short wave) እንደሚከተለው ይተላለፋል ፤

| ቀን | ሞገድ | ሰዓት | አቅጣጫ |
|---|---|---|---|
| ሐሙስ | 19 ሜትር ባንድ<br>15.365HZ | በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር<br>ከምሽቱ 1 እስከ 2 ሰዓት | ምስራቅ አፍሪካ<br>ኢትዮጵያ |
| ዓርብ | 31 ሜትር ባንድ<br>9855kHz | በአሜሪካ ሰዓት አቆጣጠር<br>9.00p.m. - 10.00pm | ሰሜን አሜሪካ<br>ምስራቃዊ ጠረፍ |
| እሁድ | 49 ሜትር ባንድ<br>5.910kHz | በአውሮፓ ሰዓት አቆጣጠር<br>9.00a.m-10.00am (10.00-11.00a.m ለብሪታንያ ) | ምዕራብ አውሮፓ |

አድራሻችን፣
አስተያየት፣
ትችት፣ ወዘተ
ካላችሁ,

Radio Rainbow ,
c/o P.O .Box 140104
53056 Bonn , Germany
Fax : 0049 228 612381

GRAPECA ሰኢአቀ RAGPEHA
Groupe de Recherche et d'Action pour la paix en Ethiopie et dans la Corne de l' Afrique
Research and Action Group for peace in Ethiopia and the Horn of Africa
ሰላም ለኢትዮጵያና አፍሪካ ቀንድ የምርምርና የተግባር ቡድን

የኢትዮጵያን ጉብኝት መሰረዛቸው አበረታች እርምጃ ሲሆን ፤ የዩናትድ ስቴትስ መንግሥት ላለፉት ሰባት ዓመታት ለወያነ/ኢህአደግ መንግሥት በሰጠውና አሁንም በሚሰጠው ድጋፍ አምባገነንነትን የሚያጠናክር በመሆኑ ፤ ፕሬዚደንት ክሊንተን ጉብኝታቸውን እንደሰረዙ ሁሉ በኢትዮጵያ ላይ አስተዳደራቸው ያለውን ፖሊሲ እንደገና ቢመረምሩ ለሁለቱ ሃገሮች ሕዝቦች የረጅም ግዜ ወዳጅነት አንድ ተጨባጭ እርምጃ እንደሆነ ፖለቲካ ተንታኞች ይገልጻሉ።

------------------////-----------------

# የፖለቲካና የዲፕሎማሲ አጥቂነት ሲባል......

ባለፍው ሳምንት በቀስተ ደመና ሬዲዮ የ 1992 ዓ ምን ምርጫ ለማጨናገፍ መጠንሰሱ የተገለጸለት ሤራ በእርግጥም አሳሳቢ ሤራ ነው። ወያኔ ኢህአደግ በቅድሚያ የወንበር ልክ ለመቋረጥና በተቃዋሚነት ለመሰየም ያሰፈሰፉት ኃይሎች፤ እንደዚህም በአባሪ ተባባሪነት ይህን ሤራ ለማራመድ ላይ ታች የሚሉት ባእዳን በተቀነባበረና ተከታታይነት ባለው የጋራ ትግል መጋለጥ አለባቸው። ይህ የማጋለጥ ዘመቻ ዛሬ ነገ ሳይባል ተጀምሮ ሴራው እርቃኑን ካልቀረ በትጥቅም ሆነ በሰላማዊና ህጋዊ ዘዴ በተቃዋሚነት የተሰለፉ ዜጎች እጅግ አሸጋሪ ሁኔታ ላይ እንደሚወድቁ ግልጽ ነው።

ፓርላሜንቱን ሙሉ በሙሉ እየተቆጣጠረ ነጻ ምርጫ አካሄጃለሁ ለማለት ዓይኑን ያላሸው ወያኔ 20 ከመቶ ተቃዋሚዎች ተሰይመው የሚቀመጡበት ምክር ቤት ለማቋቋም ከቻለ በድፍን ዓለም ተወዳዳሪነት የሌለው ዴሞክራሲያዊ ምርጫ አካሄጃለሁ ከማለት እንደማይመለስ የታወቀ ነው። ከዚያ በኋላም የሚከተለው አስቸጋሪ ትግል የዚያኑ ያህል ግልጽ ሆኖ ከዛረው ይታየናል።

**ሴራው ከወዲሁ በጋራ ትግል ካልተጋለጠ ከዚያ ወዲያ በትጥቅ ትግል የተሰማሩት ዜጎች የሃገሪቱን ህጋዊና ዴሞክራሲያዊ ሂደት አሻፈረን በማለት በውንብድና የተሰማሩና ከራሣቸው በቀር ማንንም የማይወክሉ ሽብር ፈጣሪና ደም ጠማሽ ኃይሎች ተብለው ይፈረጃሉ። ሰላማዊ በሆነ መንገድ በሃገር ውስጥ አስቸጋሪውን ትግል ለማራመድ የሚሞክሩ ዜጎችም እንደዚሁ የህዝቡን ዴሞክራሲያዊ ፍርድ የፈሩ ማንንም የማይወክሉ አክራሪዎች ተብለው ለከፍተኛ ጭቆና የሚጋለጡበት ሁኔታ ይፈጠራል። በውጭ ያሉ ተቃዋሚዎች ደግሞ የሃገራቸው ተጨባጭ ሁኔታ ያልገባቸው ስደተኛ ፖለቲከኞች እየተባሉ ተአማኒነት ሊያጡ የሚችሉበት ሁኔታ ይፈጠራል።**

ይህንን ሤራ ለማጋለጥ ተቃዋሚ ኃይሎች የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ዘመቻ መክፈትና ማካሄድ እንዳለባቸው ስምምነት ያለ ይመስለናል። ግን ደግሞ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ዘመቻ ሲባል ምን ማለት ነው?

የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ዘመቻ ሲባል አሁን እንደተያዘው በኢትዮጵያ ህዝብ ፊት የወያኔን ፖለቲካና ግፍ ማጋለጥ፤ የኢህአደግን ፖለቲካና ግፍ በመቃወም ሊወሰን አይችልም። የዲፕሎማሲ ዘመቻ ሲባልም አሁን እንደተያዘው በባእድ ኤምባሲዎች፤ በባእድ ውጭ ጉዳይ ሚንስትሮች፤ በባእድ ከመንግሥት ውጭ የሆኑ ድርጅቶች ዙሪያ ስለኢህአደግ ፖለቲካና ግፍ እየዞሩ ማስረዳት፤ በየፊናውና በዓላማው ስለሚካሄድ ትግሎች መተንተንና ገልጻ በማድረግ ሊወሰን አይችልም። የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ዘመቻ ስንል የዚህ ዘመቻ ዋና ገጽታ ግልጽ፤

አነስተኛና ትዓማኒነት ያለው አማራጭ ይዞ በኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ በዓለም አቀፍ ኮሚኒቲ ፊት መቅረብ ማለት ነው።

ሁለተኛ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ዘመቻ ሲባል አሁን እንደተያዘው ሁሉም በተናጥል እየዞረ የራሱን መፍትሄ፤ የራሱን ትግል፤ ሁሉም በተናጠል በራሱ ላይ የሚሰነዘረውን ጭቆና መቃዎምና ማጋለጥ አይደለም። ተቃዋሚ ሁሉ አራምደዋለሁ ከሚለው ፖለቲካ የጋራ የሆነውን አነስተኛ ዓላማ በጋራ ይዞ በኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ በዓለም አቀፍ ኮሚኒቲ ፊት የጋራ አማራጭ ይዞ ለሱ በጋራ መታገል ማለት ነው።

**ባጭሩ ተቃውሞ ማሰማትና ማጋለጥ ብቻ ሳይሆን አማራጭ ማቅረብ። አማራጭ ማቅረብ ብቻ ሳይሆን ይህን አማራጭ ይዞ በጋራ መንቀሳቀስ። ይህ ካልሆነ ምን ያህል ላይና ታች ቢባል ትግሉ ፈቀቅ አይልም። ይህ ከተደረገ ግን ከወያኔ አንጻር ሊውጠው ሊተፋው የማይችለው አቋም ይዘን እንቆማለን። የኢትዮጵያ ሕዝብም የትግል ወኔ ይቀሰቀሳል። አሉታዊ ብቻ ናቸው፤ አማራጭ ብናጣ ኢህአዴግን ለመደገፍ ተገደድን የሚሉትን ባእዳንም ይህንን አሳዛኝ ፌዛቸውን ትተው ቆም ብለው እንዲያስቡ እናደርጋቸዋለን። ይህ ሁሉ ሲሆን ደግሞ በዚያው ልክ ለዚች አገራችን ሰላምና ዴሞክራሲ የሚደረገውን ትግል ግልጽ ዓላማና አቅጣጫ ሰጥተነዋልና ያማይቀረው የድል ቀን ይፋጠናል ማለት ነው።**

......................////....................

# በአንድ ራስ አንድ ምላስ እንዲሆኑ

በሃገራችን ያለውን አሳዛኝ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ባለፈው ሳምንት በሃምሳ ገጽ ጽሁፍ የተቸው ዋና ጽ/ ቤት ኒውዮርክ የሚገኘው ሂውማን ራይትስ ወች የተባለው ድርጅት የአሜሪካን መንግሥት የሚከተለውን ፖለቲካ ጽናት አልባ መሆኑን ዘግቦ በአንድ በኩል የዚህ መንግሥት አምባሳደር ከተጨባጩ ሁኔታ ውጭ የኢህአዴግን ዴሞክራሲያዊነት ሰ ያሞከሹ በሌላ በኩል ደግሞ የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዓመታዊ ሪፖርቶች ኢህአዴግን እየነቀፉ መጻፋቸው የአሜሪካንን ፖሊሲ በአንድ ራስ ሁለት ምላስ ነው በማለት ተችተዋል።

በዓለም የቀረችው አንድ ኃያል መንግሥት አፍሪካን ሳይቀር ድፍን ዓለምን በማላበስ ላይ ያለው ዴሞክራሲና የሰው ልጅ መብት መከበር ሂደት ለዚች ሃገራችን ብቻ ተነፍጎ ህዝባችን በጨለማና ጨካኝ አገዛዝ ውስጥ እየዳከረ ሲታይ በዓለም የቀረችው አንድ ኃያል መንግሥት ለምን በአንድ ራስ አንድ ምላስ መሆን አቃታት?

ሂውማን ራይትስ ወች ለዚህ የሚሰጣቸው ምክንያቶች ሁለት ናቸው። አንደኛው አሜሪካ ከኢትዮጵያ የምትፈልገውና በማግኘትም ላይ ያለችው የኢኮኖሚ ጥቅም ነው ካለ በኋላ በዚች ሕዝቧ በጭቆናና በድህነት በሚዳክርባት አገራችን ባለፉት ዓመታት ከመቶ ሃያ በላይ የአሜሪካ ኩባንያዎች ተተክለው ጥቅም እያካበቱ መሆኑን ድርጅቱ ዘግቧል። ሁለተኛ ምክንያት ብሎ የሚያቀርበው የስትራቴጂ ጥቅም ምክንያት ነው። እንደ ድርጅቱ አባባል አሜሪካ ኢትዮጵያን የሱዳንንና የሌሎች ሙስሊም አክራሪ ኃይሎች ግፊት ለመቋቋምና በሱማሊያና በአጠቃላይ የተረጋጋ ሁኔታ ለመፈጠር ልትጠቀምበት ትፈልጋለች።